# አመፅ ለምን?

## ለምን ሰላም አይሆንም?

አመፅን ለማስወገድ በታቀደው የአሥር ዐመት ጊዜ ውስጥ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ያሉ ግለሰቦችና ቡድኖች እንዲያስቡበትና እንዲተገብሩ ለማገዝ የተዘጋጀ የጥናት መመሪያ::

በቤተ ክርስቲያን ያሉ
ግለሰቦችና ቡድኖች
በአስር ዓመታት
ዓመፃን ማስወገድ
የሚረዳ የጥናት
መመሪያ

# ዓመፃ ለምን?

# ለምን ሰላም አይሆንም?

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| በዚህ የጥናት መመሪያ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል | **1** |
| ዓመፃ የግድ መምጣት ያለበት ጉዳይ ነውን? | **7** |
| ኃይልን ወይም ሥልጣንን እንዴት መጠቀም አለብን? | **15** |
| የፍትሕና የጽድቅ ሕይወትን መኖር የሚቻለው እንዴት ነው? | **23** |
| ምን ዓይነት ማንነት? | **31** |
| ምን ማድረግ ይኖርብናል? | **38** |


**በዚህ መጽሐፍ የቀረቡ ሐሳቦች በሙሉ የጸሐፊው እንጂ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ ይፋ መግለጫን የሚወክሉ አይደሉም:: ጽሑፉ የቀረበው በሚቀጥሉት አሥራ ዓመታት ዓመፃን በማስወገድ ረገድ ንቁ ተሳታፊ እንድትሆኑ ለማበረታታት ነው::**


Written by Diana Mavunduse and Simon Oxley.
ISBN 2- 8254-1371-2
Published by the World council of churches

**Translated by:-**
**EECMY Peace Office**

**ትርጉም:-**
**በኢ.ወ.ቤ.ክ. መካነ ኢየሱስ ሰላም ቢሮ**

# በዚህ የጥናት መመሪያ እንዴት ጠቀም እንደሚቻል

በዚህ የጥናት መመሪያ መጠቀም ዓመፃን በማሸነፍ ረገድ ለሚቀጥሉት አሥር ዓመታት በምታደርገው እንቅስቃሴ (Decade to overcome Violence- Dov) ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፤ እርቅና ሰላምን ለማስፋፋትም ንቁ ለመሆን ያስችላል::

ከዚህ የጥናት መመሪያ የምናገኛቸው ቁም ነገሮች:-

- በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ዓመፃን ማሸነፍ (Dov) ሲባል ምን ማለት እንደሆነ መሠረታዊ ግንዛቤ ያስጨብጣል:
- በጥልቀት ልናስብባቸው የሚገቡ አራት ቁም ነገር አዘል ጭብጦችን ያቀርባል፤

- እንዴት እርምጃ መውሰድ ወይም ተሳትፎ ማድረግ እንደሚገባ ያመለክታል፣
- ተጨማሪ ምንጮችን ለማግኘት የሚረዳ መረጃን ይሰጣል፤
- በመጨረሻ ሁለት ጸሎቶች ያቀርባል (በመጽሐፉ ጀርባ)::
  እያንዳንዱ ምዕራፍ በጥልቀት ልናስብበት የሚገባ ሦስት ክፍሎችን ይዘአል:-
- ከራስህ ተሞክሮ ወይም ልምምድ በመነሳት ወደ ርዕስ ጉዳዩ መግባት የሚያስችልህ መልመጃ፤
- በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ውይይት ለማድረግ ተነሳሽነት የሚሰጥህ ሐሳብ፤



- ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚሆኑ ነጥቦች፤

ይህን ጽሑፍ ካለህበት ሁኔታ ጋር ለማጣጣም በምታደርገው ሙከራ ሦስቱንም ክፍሎች ከፍተኛ ትኩረት ልትሰጣቸው ይገባል:: በጥልቀት ልታስብባቸው ከሚገቡ ነጥቦች በመነሣት የሚቀጥለው እርምጃህ ምን መሆን እንዳለበት ወደ ማሰብ መሸጋገር እንዳለብህ አስብ:: ይህ የጥናት መመሪያ በግልህ ልትጠቀምበት ትችላለህ፤ ይሁን እንጂ ከሌሎች ጋር እየተወያያችሁ ብታጠኑት ይበልጥ ሊጠቅማችሁ እንደሚችል አጠንክረን እናሳስባለን:: ይህ ደግሞ በጥንቃቄ ዝግጅት ማድረግን ይጠይቃል:: ቡድኑን ለመምራት ያስችለው ዘንድ ቢያንስ ከመካከላችሁ አንዱ ጽሑፉን በሚገባ ማጥናት ወይም አጠቃላይ ግንዛቤውን መጨበጥ እንደለበት ግልጽ ነው:: ለማጥናት ስትሰበሰቡ የእንኳን ደህና መጣችሁ ዓይነት አቀባበል ወይም ተሳታፊዎችን ዘና የሚያድርግ ድባብ መኖሩ መልካም ነው:: ክበብ ወይም ክብ ሠርታችሁ መቀመጡ ፊት ለፊት እየተያያችሁ ለመነጋገር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል:: ካለህበት ነባራዊ ወይም ተጨባጭ ሁኔታ በመጀመር የውይይቱን አድማስ እያሰፋህ ሂድ:: ተሞክረአቸውን ወይም ልምምዳቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት እንዲናገሩ ለተሳታፊዎች ዕድል ስጣቸው፤ ይሁን እንጂ ይህ አንዳንዶቹን ሊጎዳ ወይም ሊያሳምም እንደሚችል ከወዲሁ ግምት ውስጥ አስገባ:: መስማት የመናገርን ያህል አስፈላጊ መሆኑን አስታውስ፤ ጎጂ ቃላት አካልን የሚያሳምሙ ነገሮችን ያህል አፍራሽ መሆናቸውን አትርሳ:: አብራችሁ የምታሳልፉት ጊዜ ጸሎትን መሠረት ያደረገ ይሁን::

በጥልቀት ስታስቡ፤ የሐሳብ ልውውጥ ስታደርጉና
ለተግባር ስትነሣሡ ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን::

## *የተሳትፎ ጥሪ*

«ሰላም ዕለት ዕለት የምትሠራው፤ በዓላማ የምታደርገው፤ የምትሆነውን ለሌሎች የምትሰጠው እንጂ የምትመኘው አይደለም» (እማሆይ ቴሬዛ)

ከላይ የተመለከትነው ጥቅስ ሰላም ሰጪዎችና ሰላም አድራጊዎች እንድትሆን አበክሮ የሚያሳስብ ነው:: ሰላም ያለው በውጣችን መሆኑንም ያስገነዝባል:: ይሁን እንጂ ሰላም እንዲኖረን ከተፈለገ አብረን መሥራትና አብረን መንቀሳቀስ ይኖርብናል:: ዓመፃን ለማሸነፍ አሥር ዓመታት የተሰኘውን እቅድ ዕርቅና ሰላምን ማምጣት ከሚሹ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ዛሬውኑ መጀመር እንዳለብን የሚያነሳሱንም በዚህ ዓይነት ነው::

አንዳንዴ እኛ ራሳችን ሳናውቀው ለዓመፃ መስፋፋት አስተዋጽኦ ልናደርግ እንችላለን:: አብረን መሥራቱ ይህን እንድንገነዘብና በአካባቢያችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዓመፃን ተያያዥነት ለመረዳት ያስችለናል የምንለው በዚህ ምክንያት ነው:: በዘሁኑ ጊዜ ዓለም አቀፍ ዕርቅን ለማምጣት በሚፈልጉ ወገኖች አጋዥነት ሰላምን ለማስገኘት የሚያስችሉ አዳዲስ ምሳዎችን ተግባር ላይ ማዋል ይቻላል::

ዓመፃ መላውን ዓለም ያዳረሰና ብዙ ገጽታዎች ያሉት በመሆኑ እያንዳንዱ አባል ቤተ ክርስቲያን በአካቢቢም ሆነ በማኅበራዊ፤ በክልልም ይሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ፤ በአሥርት ዓመቱ እንቅስቃሴ ተሳትፎ ማድረግ የሚችልበትን ትክክለኛ መንገድ በግሉ መገንዘብ ይኖርበታል:: በሚቀጥሉት አሥርት ዓመታት ዓመፃን ማጥፋት የተሰኘውን እቅድ በተመለከተ በተደጋጋሚ የሚነሳ ጥያቄ «የዓመፃን ዙሪት ማስወገድ የሚቻለው እንዴት ነው?» የሚል ነው:: በከፊልም ቢሆን ይህ የጥናት



መመሪያ የሚሰጠው መልስ «የድንቁርናን» ወይም የአላዋቂነትን አዙሪት በምናስወግድበት መንገድ» የሚል ነው:: የአላዋቂነትን አዙሪት ወይም ተደጋጋሚነት የምናስወግደው ሰዎችን በማስተማር ነው::

## *በአሥርት ዓመታት ዓመፃን ማስወገድ የተሰኘው እቅድ እንዴት ተጀመረ?*

ምንም እንኳን በ20ኛው ክፍለ ዘመን የታየው አስደናቂ ቴክኖሎጂያዊ ግኝት በሰዎች መካል ሊኖር የሚገባውን እርስ በርስ መከባበር አሻሽሎአል ብለን ብገምትም ዛሬም ቢሆን የጎሳ፤ የዘር፤ የክልል የኢኮነሚና የጾታ ግጭት መኖሩ ከገጠሙን አሳዛኝ ሁኔታዎች አንዱ ሆኖአል:: ቴክኖሎጂካዊ ግኝቶቻችን እነዚህን መሠረታዊ ችግሮች አላስወገዱልንም::

ቆም ብለን ያለፈውን ክፍለ ዘመን ታሪክ የምንቃኝበት ጊዜ ቢኖር አሁን ነው:: በሚቀጥሉት አሥርት ዓመታት ዓመፃን ማስወገድ (Dov) ዕቅድ የተጸነሰው በ1988 ዓ.ም. በሐራሬ ዚምቧቤ ተደርጎ በነበረው ስምንተኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ ሲሆን፤ ዓላማው ወደፊት ለሚመጣው ትውልድ ለቀረበው የሰላም ጥሪ ምላሽ መስጠት ነበር:: ያለፈውን ምዕተ ዓመት በትዝታ ዓይን እንድንቃኝም አድርጎና:: የካቲት 4/2001 የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ ያሳለፈው መልዕክት አዲሱን ምዕተ ዓመት አስመልክቶ የሚከተለውን ተስፋ መሠረት ያደረገ ሲሆን፤ ይህ ማዕከላዊ ኮሚቴው አንግቦ የተነሳው ራዕይ:- «የራሳችንን ሕይወት፤ ማኅበረሰባችንን፤ የምንኖርበትን ዓለምና መላው የተፈጥሮ ሥርዓትን እየናጠ ያለው አጣዳፊ ችግር ያሳሰበን ወገኖች ከአራቱም የምድር ዳርቻዎች በዚህ ሥፍራ ተሰብሰበናል:: ለሕዝቦቻችን ጭንቀትና ዋይታ ምላሽ

ለመስጠትና ፍትሕን ያገናዘበ ሰላም ይመሠረት ዘንድ ይህን የአሥር ዓመት ዕቅድ ሥራ ላይ አውለናል» የሚል ነበር::

ይሁን እንጂ የአሥር ዓመቱ ዕቅድ ቀድሞውኑ የተዘጋጁ መርሐ ግብሮችን ማስፈጸሚያ ሳይሆን ሰላምን በመፍጠር ረገድ እያንዳንዱ ክርስቲያን በተቀበለው ጥሪና ባለው ስጦታ አማካይነት አስተዋጽኦ እንዲያደርግ፤ አንዱ ከሌላው እንዲማርና እንዲሠራ የቀረበ ግብዣ ነው:: ጥሪው የግለሰቡን ሕይወት ከመለወጥ ያለፈ ነው:: ዓላማው ከእያንዳንዱ ግለሰብ በስተጀርባ ያለውን የዓመፃ ሥረ መሠረት መፍትሔ መሻት ላይ ያነጣጥራል:: በመጀመሪያ ደረጃ ለዓመፃ መነሻ ዋናው ምክንያት በሰዎች መካከል እኩልነት አለመኖሩ ነው፤ የአሥር ዓመቱ ዕቅድ ደግሞ ለችግሩ አንኳር ምክንያት መፍትሔ መስጠትን ግምት ውስጥ ያስገባል::

ከሁሉም ይልቅ ደግሞ በግለሰብም ይሁን በአብያተ ክርስቲያናት ደረጃ ፍትሕ ይሰፍን ዘንድ ከእግዚአብሔ የተቀልነው ጥሪ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ምን እንደሆነ ያለንን ግንዛቤ የምንፈትሽበት ጊዜ ይሆንልናል::

ዓመፃ ሊኖር የቻለበትን ዋነኛ ምክንያት መረዳት ከቻልን በራሳችን ሕይወትም ሆነ በዙሪያችን ባለው ዓለም መጠኑን ለመቀነስ ምን ማድረግ እንዳለብንና እንደሌለብን መረዳት እንችላለን፤ በአንጻሩም ዕርቅና ይቅር የመባባል መንፈስ የሚፈጠርበትን መንገድ መረዳትና ያንንም ማዳበር እንችላለን ማለት ነው::

የአሥር ዓመቱን ዕቅድ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ የዓመፃ ሥረ መሠረት ናቸው ብሎ የሚያስባቸው አራት ዋና ዋና ነጥቦችን አቅርቦአል:: እነዚህ ዋና ዋና ነጥቦች በ2000 - 2001 በተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናት ከተደረገው ጥናት የተወሰዱ ናቸው::



አራቱ ዋና ዋና ነጥቦች:-

- የዓመፃ መንፈስና ሥነ ምክንያት፤
- ኃይልንና ሥልጣንን አለአግባብ መጠቀም፤
- የፍትሕ መጓደል፤
- ሃይማኖታዊ ማንነትንና ሕዝባዊ መብትን መዳፈር::

በመሠረቱ እነዚህን ርዕስ ጉዳዮች ያቀረብነው ለምሑራዊ ምርምር ብቻ ሳይሆን፣ ዓመፃን በማሸነፍ ረገድ ለሚጠብቀን ተግዳሮት አብያተ ክርስቲያናት ግንዛቤ እንዲጨብጡና ዘላቂ መፍትሔ በማስገኘት የራሳቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ለማገዝ ነው::

ይሁን እንጂ የእነዚህ አራት ጉዳዮች ገጽታ ወይም በማሕበረሰቡ ውስጥ ያላቸው መስተጋብር እያንዳንዱ አብያተ ክርስቲያን ባለበት ስፍራና ሁኔታ ሊወሰን ይችላል:: ስለዚህም እነዚህን ዓቢይ ነጥቦች የምንመረምረው አብያተ ክርስቲያናቱ ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት መሆን አለበት ማለት ነው::

# ዓመፃ፤ የግድ መምጣት ያለበት ጉዳይ ነውን?

## *መንደርደሪያ:-*

እስቲ በምትኖርበት አገር ያሉ መጽሔቶችና ጋዜጦችን ተመልከት። በተለያየ አካባቢ ስለ ተቀሰቀሰ ዓመፃ ሪፖርት የሚያቀርቡ ምን ያህሉ ናቸው? ሰፊ ሽፋን የተሰጣቸው ዓመፆች ምን ዓይነቶቹ ናቸው? ጋዜጦቹ ወይም መጽሔቶቹ ወይም ሌሎች መገናኛ ብዙኃን በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን ዓመፃ በትክክል ወይም ሚዛናዊ በሆነ መልኩ አቅርበዋል ብለህ ታስባለህ? በማኅበረሰብህ ውስጥ ስላየኸው አንተ ራስህም ስላለፍክበት ዓመፃ ወይም አሳዛኝ ሁኔታ ብዙ የምትናገረው ሊኖርህ ይችላል። ይሁን እንጂ፤ አንዳንድ የዓመፃ ተጠቂዎች ሰለ ጉዳዩ እንዲነገርባቸው ወይም ለውይይት እንዲቀርብ ላይፈልጉ ይችላሉና እንዲህ ስላሉ ነገሮች ስትናገር ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብሃል።

እንደ ቴሌቪዥን ወይም ሬዲዮ ካሉት መገናኛ ብዙኀን የዓለምን ዜና ተከታተል። ስለ ዓመፃ የሚያቀርቡት የትኞቹ ዘገባዎች ናቸው? ስለምን ዓይነት ዓመፀ ነው ያቀረቡት? እነዚህ ነገሮች ዐቢይ ዜና መሆን የቻሉት ለምን ይመስልሃል?

በሲኒማና በቴሌቪዥን ምን ዓይነት ፊልሞች እየታዩ ነው? ወጣቶች የሚያዘወትሩት ምን ዓይነት የኮምፒዩተር ጨዋታዎችን ነው? እንደ መዝናኛ ወይም ጊዜ ማሳለፊያ የምትጠቀምበት ምን ያህል ከዓመፃ ጋር የተያያዙ ነገሮችን አካትቶአል?



# *ስለ ዓመፃ በጥልቀት እንድታስብ የሚረዱህ ነጥቦች:-*

> *ዓመፃ እርስ በርስ ያራርቃል፤ በዚያው ልክ ደግሞ ዓመፃ ያሰባስባል።*
> *ዓመፃ ያስደነግጣ፤ በዚያው መጠን ደግሞ ዓመፃ እንደ መዝናኛ ሊሆንልን ይችላል።*
> *ዓመፃ ያጠፋናል፤ በዚያው ልክ ደግሞ ዓመፃ ይከላከልልናል።*

እኛ የሰው ልጆች ዓመፃን በተመለከተ ሁለት የተለያየ ዓይነት አስተሳሰብ ያለን ይመስላል። ያም ሆኖ ግን ብዙዎቻችን ዓመፃ ጨርሶ የማይቀርና ማስወገድ የማይቻል ጉዳይ እንደሆነ እናስባለን። ዓለማችን ያለችበትንና፤ ማኅበረሰቡና እኛ ራሳችን ያለንበትን ሁኔታ ተልክተን ወደ እንዲህ ዓይነቱ መደምደሚያ ብንደርስ ብዙ የሚያስገርም ላይሆን ይችላል። እኛ ራሳችን ያለንበትን ሌላው ወገናችን ላይ ማድረስ የምንችለውን ጥፋት ግምት ውስጥ በማስገባት የስው ልጅን ባሕርይ ወይም ተፈጥሮ በተመለከተ ጽልመተኛ አቋም መያዝ በጣም ቀላል ነው።

ይሁን እንጂ እምነት የሰው ልጅ ባሕርይ በተለየ ሁኔታ ማየት የምንችልበት መንገድ መኖሩን ያሳስባል። የሰው ልጅ በፍጥረታት ውስጥ ያለውን ስፍራ በማጤን ዘማሪው እጅግ የከበርን የእግዚአብሔር ፍጡራን መሆናችንን አስመልክቶአል (መዝ. 8)። ሰዎች የተፈጠሩት በእግዚአብሔር መልክና አምሳል መሆኑ ግልጽ እስከ ሆነ ድረስ በተፈጥሮአችን ያለውን መለኮታዊ ነጸብራቅ ማስተዋል ይኖርብናል። የሰው ልጅን በተመለከተ ለተለያዩ አፍራሽ ወይም አሉታዊ አመለካከቶች እጅ መስጠት በክርስቶስ በኩል የተገለጸውን አምላክ ሳይሆን፤ በባሕርዩ ንፉግን ፈራጅ

የሆነውን፤ በዓመፃ ደስ የሚያሰኘውን አምላክ ማምለክ ማለት ነው።

እንዲህ ሲባል ግን ሁሉም መልካምና አስደሳች እንደሆነ በማሰብ የራሳችን ፈጠራ ዓለም ውስጥ መኖር አለብን ማለት አይደለም። ስለ ሰው ልጅ ዓመፀኛ ባሕርይ ያለን አመለካከት ተለውጦ የሰላምና የፍቅር እንዲሆን ከተፈለገ አሁን ያለውን ብቻ ሳይሆን መሆን የሚችለውን ለማሰብ የዕይታ አድማሳችንን ማስፋፋት ይኖርብናል። ያም ሆኖ ግንዛቤያችን ሐቅን ያገናዘበና ሙሉ በሙሉ ተስፋን መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል።

ምናልባትም እኛ ራሳችን ሳናውቀው የዓመፃ ተባባሪዎች መሆናችንንና ከዚህም የተነሳ የሚኖርብንን ኃላፊነት በመቀበል መነሣት ይኖርብን ይሆናል። በዚህ ዓለም ስላለው ችግር የተቀሩት ቤተ ሰቦቻችን አባሎች፤ የቤተ ክርስቲያን፤ የመንግሥት ወይም ዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም የፈጠው እንደሆነ እናስባን። ምናልባትም የራሳችንን አፈጣጠር ወይም ያለንበትን አካበቢ ተጠያቂ እናደርግ ይሆናል። እንዲህ ሲባል ግን በዓመፃ የተሞላ ዓለምን በማስገኘት ረገድ እነዚህ ነገሮች ያላቸውን ተፅዕኖ አይተን እንዳለየ እናልፋቸዋለን ማለት አይደለም። ያም ሆኖ ግን የራሳችንን ኃላፊነት እንዳንወጣ ሰበብ ወይም ምክንያት ሊሆኑን አይገባም። ምናልባት እኛ ራሳችን የተለያዩ ዓመፃ ተጠቂዎች እንሆን ይሆናል፤ እንዲህ ያለ ስሜት ካለን ሁለት ችግሮች ፊት ለፊታችን ይጋረጣሉ። አንደኛው ሁኔታዎችን ለመለወጥ የሚያስችል አቅም እንደሌለን

አምነን መቀበል ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ተጠቂዎች ውሎ አድሮ አጥቂዎች እንደሚሆኑ በሰዎች ሥነ ልቦና ውስጥ ያለ ነገር ይመስላል፤ ለምሳሌ ያህል የተለያየ ችግርና መከራ የደረሰበት ልጅ እርሱ ራሱ ችግር ፈጣሪ ወላጅ ይሆናል፤ አንድ ወቅት ተጨቁነው የነበሩ ሕዝቦች እነርሱ ራሳቸው ጨቋኞች ይሆናሉ የሚለውን አስተሳሰብ እንደ መሠረታዊ እውነት የመቀበል አዝማሚያን ማዳበር



ነው። ዓመፃን ተግባር ላይ የምናውልበት የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም ለአስተሳሰባችን አማራጭ እንዲሆኑልን ከእነዚህ ጥቂቶቹን እንመልከት፡-

**ሌሎች ሰዎች ፈቃዳችንን እንዲፈጽሙልን ጫና ስናደርግ ዓመፃ ይፈጠራል።**

ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ ሊሆነን የሚችል ባርነት ነው፤ ዛሬም ቢሆን ለብዙዎች የባርነት ዘመን ያለፈ ጊዜ ታሪክ አይደለም። የተወሰኑ ሰዎች የተለያዩ ሰዎችን ፈቃድ የሚያሚሉበት ሥርዓት መፍጠር የግድ እንደ ባሪያ መሸጥ መለወጥና ከአንዱ ወደ ሌላው ክፍለ ዓለም መወሰድ የለባቸው። የሌላው ሰው ፈቃድ ተገዢዎች እስከሆኑ ድረስ ባሪያዎች ሆነዋል።

**ሰዎች በሌሎች ላይ ጥገኛ ስለሚሆኑበት መንገድ ያን አማራጭ አስተሳሰብ ምንድን ነው?**

**ሌሎች የእኛን ሐሳብ እንዲቀበሉ ተፅዕኖ የምናደርግ ከሆነ ዓመፅ መኖሩ የግድ ነው።**

ይህን ተግባር ላይ የምናውለው የተለያየ ሽፋን በመስጠት ሊሆን ይችላል፤ ምናልባት «ጌታን እንዲቀበሉና ነፍሳቸው እንድትድን» የሚል ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ እኛ

ያገኘነውን ማኅበራዊ ወይም ኤኮኖሚያዊ «ጠቀሜታ» እንዲያገኙ ያለ ውዴታቸው የምናሳድርባቸው ግፊት ሊሆን ይችላል፤ በዚህም ይሁን በዚያ፤ ሌሎች እምነታችንን እንዲቀበሉና እኛ በምንኖረው ዓይነት እንዲኖሩ ጫና ስናደርግ ለተለያዩ ዓመፃዎች መቀስቀስ ምክንያት ሊሆኑ ይችላል።

የሰዎች አመለካከትና አስተሳሰብ እንዲከበር የምታቀርበው አማራጭ ምንድን ነው?

የራስ ያልሆነ ነገርን ከሌሎች መውሰድ ዓመፃ ሊያነሳሳ ይችላል፡፡ ይህችን ትንሽ መጽሐፍ እያነበቡ ካሉት በጣም ጥቂቶች ምናልባት ባንክ የዘረፉ ወንጀለኞች ይሆኑ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ሰፋ ባለ መልኩ ስመለከተው ጥቂቶች እንዲጠቀሙ ሲባል ብዙዎች የሚመዘበሩበት ዓለም አቀፍ ኤኮኖሚያዊ ሥርዓት አጣብቂኝ ውስጥ መሆናችን ለማንኛችንም ግልጽ ይሆናል፡፡ በዚህ ዘመን እየተፈጸሙ ያሉ ጦርነቶችና ግጭቶች አልማዝንና ነዳጅ ዘይትን ለመበዝበዝ የሚደረጉ ናቸው፡፡

የተፈጥሮ ባለ አደራዎች እንጂ፤ ባለ መብት አለመሆናችንን ለማሳየት የምታቀርበው ሌላ አማራጭ ምንድን ነው?

## ወንጀለኞችን መቅጣት

ማኅበረሰብ ወይም ግለሰብ ላይ በደል የሚፈጽሙ ወንጀለኞችን መቅጣር በተመለከተ ብዙውን ጊዜ የሚርቡ ሁለት ምክንያቶች በአንድ በኩል ለጥፋቱ ተገቢውን ቅጣት ለመስጠት ሲሆን በሌላ በኩል ግን ለወንጀለኛው እርምት እንዲሆን ነው ቢባልም ቅድሚያ

ሲሰጠው የምናየው ግን ለመጀመሪያው ምክንያት ነው፡፡ ወንጀለኛው የእጁን ሲያገኝ ማየት አንድ ዓይነት እርካታ ያስገኝልናል፡፡ ይሁን እንጂ «ዓይን ያጠፋ ሁሉ፤ ዓይኑ እንዲጠፋ ቢፈረድበት ኖሮ ዓለማችን የእውራን ዓለም ትሆን ነበር» በማለት ማሕተማጋንዲ መናገራቸውን እዚህ ላይ መጥቀሱ አግባብነት ይኖረዋል፡፡

አጥቂውም ሆነ ተጠቂው ሞራላዊ ተሐድሶ ያገኙ ዘንድ ምን ዓይነት ፍትሕ መኖር አለበት ትላለህ? ለራሳችንና ለሌለች አቅመ ቢሶች ለመከላከል ስንል



የምንወስደው እርምጃ
የራሳችንና የሌሎችን መብት ለማስከበር እስከሆነ ድረስ ዐመፅ ተገቢ ነው የሚለውን አመለካከት የሚያራምዱ ወገኖች ለትክክለኛነታቸው እንደ ማረጋገጫ የሚያቀርቡት ይህን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ግለሰጉም ይሁን ማኅበረሰብ፤ ዓመፃን በዓመፃ መመለሱ ይዋል ይደር እንጂ ማኛውንም ወገን መጉዳቱ አይቀርም፡፡

የግለሰቡም ይሁን የማኅበረሰብ ዋስትና ይከበር ዘንድ አማራጭ መንገድ ሊሆን ይችላል የምትለው ምንድን ነው?

የዓመፅ መንገድን ለምን እንደምንከተል ሌለች ተጨማሪ ምክንያቶችን ታስብ ይሆናል፤ ከራስህም ሆነ ከሌሎች ተሞክሮ በመነሣት ሌሎች ብዙ ምሳሌዎችን ማቅረብ ትችል ይሆናል፡፡ ከእነዚህ መካከል ጥቂቶቹን በሌላ ክፍል ለመመልከት እንሞክራለን፡፡

ዓመፃን መጠቀም ተፈጥሮአዊና መሆን ያለበት ጉዳይ እንደሆነ የምናስበው ሌሎች አማራጮችን ማየት ስላልቻልንና ለበጎ ነገር ተነሣሽነት ሊሰጠን የሚችል እምነት ስለ ሌለን ሊሆን ይችላል፡፡
ከመጽሐፍ ቅዱስ፤ ከባሕላችን፤ ከአምልኮ ሥርዓታችን፤ ከመንፈሳዊ ሕይወታችን፤ ከተሞክሮአችን፤ ከድርጊታችንና ከሌሎች ጋር ካለን ግንኙነት ወይም ከእምነታችን ከምናገኘው ግንዛቤ ምን ዓይነት አማራጭ መንገድ ማቅረብ ይቻላል?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

በንጉሥ ናቡከደነፆር በምርኮኝነት ወደ ባቢሎን ለተወሰዱ ለኢየሩሳሌም ሰዎች ነቢዩ ኤርምያስ በጣም የሚገርም መልእክት ጽፎላቸው ነበር::

### 🕮 ኤርምያስ 29:4-7 አንብብ

ኤርምያስ ለሕዝቡ የነገራቸው የምርኮው ዘመን እስኪያበቃ ድረስ የዕለት ዕለት ኑሮአቸውን ብቻ እንዲኖሩ አልነበረም:: ይልቁንም በምርኮ ያሉበትን አገር እንደ ራሳቸው አገር በማየት ቤቶችን እንዲሠሩ፤ እርሻን እንዲያስፋፉና ቤተሰብን እንዲመሰርቱ ሲመክራቸው ነው የምንመለከተው:: ይህ አባባሉ አስገርሞአቸው ከሆነ ቀጥሎ የተናገረው ደግሞ ምናልባት ሳያስደነግጣቸው እንደማይቀር ማሰብ ይቻላል:: ከቁጥር 7 እንደምንመለከተው በምርኮኝነት ለነበሩበት ከተማ ሰላምና ደኅንነት አጥብቀው እንዲጸልዩና ይህንኑ እውን ለማድረግ በርትተው እንዲሰቱ ያሳስባቸዋል:: መልካም ሊሆንላቸው የሚችለው ለዚያች ከተማ መልካም ሲሆንላት ብቻ እንደሆነ በእርግጠኝነት ይነግራቸዋል::

እስቲ ስለ ነበሩበት ሁኔታ እናስብ፤ ሥልጣን ላይ ባለው ፖለቲካዊ ሥርዓት ተማርተዋል:: ሃይማኖታቸው ከሃይማኖቻቸው ጋር ጨርሶ በማይመሳሰል ጠላቶቻቸው መካከል እንዲኖሩ ተገድደዋል:: ማናልባትም ለእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ብዙዎቻችን የሚኖረን አመለካከት ተቃውሞ ወይም በቀልን መሠረት ያደረገ ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ ለራሳቸው መልካም የሚሆንላቸው ለጠላቶቻቸው መልካም ሲሆን በመሆኑ ይህ እውን ይሆን ዘንድ በርትተው መሥራት እንዳለባቸው ነበር ኤርምያስ ለእስራኤላውያኑ የነገራቸው::



### 🕮 ሮሜ 12:9-20 አንብብ

ጳውሎስ ይህን የጻፈው ስደት ወይም መከራ ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ ለሚያውቁ ክርስቲያኖች ነበር:: ቀኝ ጉንጭህን ለሚመታህ ሌላውን ጉንጭህን ደግሞ አዙርለት የሚለውን የጌታን ቃል መጥቀስ ቀላል ነው (ማቴ. 5:39)፤ ይሁን እንጂ በተግባር ማዋሉ ግን በጣም ከባድ ነው:: በተለይ ደግሞ ጠላቶቻችንን እንድንወድ ለሰጠን መመሪያ መታዘዝ ከዚያ የበለጠ ከባድ ነው (ማቴ. 5:44):: በቀል የእኛ ፈንታ አለመሆኑን ጳውሎስ የሚናገረው በጣም ግልጽ አድርጎ ነው:: ይልቁንም ክፉውን በመልካም ማሸነፍ አለብን:: ዓመፃ ለትክክለኛነቱ የራሱ የሆነ ምክንያት ማቅረብ ይችል ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ስለ ዕርቅ አስፈላጊነት እግዚአብሔር በጣም በላቀ ሁኔታ ተቃራኒውን ሐሳብ ያቀርባል::

የራሳችን ደመ-ነፍሳዊ ግንዛቤ የሚነግረን የሚበድሉንን መልሰን እንድንበድል መሆኑ እየታወቀ፤ እምነት ግን ተግባራዊ በሆነ መልኩ ጠላቶቻችንን እንድንወድ የሚነግረን ለምንድን ነው? የምንፈራቸውን፤ የሚንቁንና የሚጠሉንን ሰዎች በጎነትና ሰላም እየፈለግን እኛ ራሳችን እንዴት በጎነትና ሰላም ሊኖረን ይችላል?

# ኃይልን ወይም ሥልጣን እንዴት መጠቀም አለብን?

## *መንደርደሪያ*

እስቲ ስለ ኤሌክተሪክ ኃይል እናስብ:: የኤሌክትሪክ ኃይል ምን ለማድረግ ይረዳል? በኤሌክትሪክ ስንጠቀም ሊከተሉ የሚችሉ አደጋዎች ምንድን ናቸው? (ይህን ጽሑፍ የምታጠኑት በቡድን ደረጃ ከሆነ፤ ለሁለት ተከፈሉና በጥያቄዎቹና በምታገኟቸው መልሶች ተወያዩባቸው):: ጠቃሚ፤ በዚያው መጠን ደግሞ አደገኛ የሆኑ ሌሎች ነገሮችስ ምንድን ናቸው?

በቤተሰብህ፤ ማኅበረሰብህና በአገርህ መሆን ያለበትን የሚወስን ማን ነው? በዚህ ላይ ሥልጣን ያለው ግለሰብ ወይም በቡድን ወይም በፓርቲ ደረጃ ያለ አካል ሊኖር ይችላል:: ውሳኔ የማድረግ ሥልጣን ለእነዚህ ሰዎች የሰጣቸው ማን ነወው ውሳኔዎቹ መልካም ወይም መጥፎ መሆናቸውን የምትመዝኑት እንዴት ነው?

## *ኃይልን ወይም ሥልጣንን በተመለከተ በጥልቀት እንድታስብ የሚረዱ ጥቂት ነጥቦች:-*

በአጭር አነጋገር ሥልጣን ወይም ኃይል ማለት ሌሎችን የመቆጣጠር፤ ወይም በፈለጉት መንገድ ነገረችን የማስፈጸም ችሎታ ማለት ነው:: አንድ ኃይል ወይም ሥልጣን መልካም ወይም መጥፎ መሆኑን ማወቅ ከፈለግን የዚያ ኃይል ወይም ሥልጣን ምንጭ ማን እንደሆነና የሥልጣኑ ዓላማና ውጤት ምን እንደሆነ አብረን ማየት ይኖርብናል:: የኤሌክትሪኩ ኃይልን አስመልክቶ በነበረን የመክፈቻ ውይይት ኤሌክትሪኩ ኃይልን የሚያገኘው መተካት ወይም መታደስ ከሚችሉ ነገሮች



መሆን አለመሆኑ ወይም የኃይል ጣቢያዎቹ ላይ ብክለት አለማድረሱን፤ ኃይልን ለገበያ በማቅረብ ሌሎችን ለመበዝበዣ መዋል አለመዋሉን፤ ንዝረት ወይም ቃጠሎን የመሳሰሉ አደጋዎችን፤ ብርሃንን ሙቀትን በቤተ ውስጥም ሆነ በፋብሪካ የምንጠቀምባቸው መሣሪያዎችን በማንቀሳቀስ ስለሚያስገኘው ጥቅም ተወያይታችሁ ይሆናል:: ስለ ኃይል ጠቃሚነትና ጎጂነት ኤሌክትሪክ ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል፤ ይህን አስመልክቶም ሌሎች ውስብስብ ተያያዥ ጉዳዮችም ሊነሱ ይችላሉ::

ዓመፃ ማለት ኃይልን አላግባቡ ወይም አለቦታው መጠቀም ማለት ነው በሚል መልኩ ብናቀርበው ስሕተት አይሆንም:: ያ ማለት ግን፤ ማንኛውንም ዓይነት ኃይል አንጠቀምም ማለት አይደለም:: ኃይልና ዓመፅ የሚለያዩበት አንዱ ነጥብ እዚህ ላይ ነው:: ዓመፅ የሌለበትን ዓለም ተስፋ ማድረግ እንችላለን ኃይል የሌለበት ዓለም ግን በፍጹም የማይታሰብ ነው:: ምንም እንኳ ደካሞች ወይም ፋይዳ ቢሶች ነን ብለን ብናስብም፣ በግለሰብም ይሁን በቡድን ደረጃ አንዳንድ ነገሮችን ማድረግ የሚያስችለን ኃይል ይኖረናል:: ያንን ኃይል ግን መጥፎ ሁኔታዎችን ለማስተካከል ወይም ፈውስና እርቅን ለማስገኘት ልንጠቀምበት እንችላለን:: ኃይልን ሳንጠቀም፤ አንዳች መልካም ነገር ማድረግ አይቻልም:: «ክፋት ድል ማድረግ የሚችለው መልካም ሰዎች ምንም ያላደረጉ እንደሆነ ነው» የሚል አባባል አለ::

ኃይል ወይም ሥልጣን የሚመጣው ከየት ነው? አንዱ መልስ ከእግዚአብሔር ነው የሚለው ሊሆን ይችላል:: እንዲህ የምንል ከሆነ እግዚአብሔር የማንኛውም ነገር ፈጣሪና ኃይልን የምንቀበለው ከመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ተረድተናል ማለት ነው:: አንዳንዶች ደግሞ ኃይልን ከእግዚብሔር ባሕርይ ወይም ተፈጥሮ ጋር

ሊያያይዙት ይፈልጋሉ። ስለ ዓመፃ አስፈላጊነት የሚናገሩ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦችን በመጥቀስ እግዚአብሔር የሚፈልገው እንዲህ እንድናደርግ ነው ወደሚል መደምደሚያ እንደርስ ይሆናል። አንዳንዴም ባለን ኃይል አላግባብ መጠቀማችን ትክክል እንደሆነ ለማሳየት በእግዚብሔር ላይ ለማሳበብ እንሞክር ይሆናል። እንዲህ የምናሳብብ ወይም የምናደርግ ከሆነ ደግሞ እምነትን በተመለከተ ነገሮ ተዘበራርቀውብናል ማለት ነው። ምንም እንኳ ሆን ብለን ባይሆንም እግዚአብሔርን የራሳችን ዓመፀኛ ባሕርይ ተካፋይ አድርገነዋል ማለት ነው። ይሁን እንጂ የትንሳኤው ኃይል፤ በምንም ዓይነት ከጡንቻ፤ ከሚሳይል ወይም ከኤኮኖሚያዊ ኃይል ጋር በፍጹም ተመሳሳይ አይደለም።

በእያንዳንዳችን ውስጥ ኃይል አለ - ምናልባትም በእግዚብሔር መልክና አምሳል መፈጠራችን እውነት ሊሆን ከሚችልበት ምክንያት አንዱ ይህ ሊሆን ይችላል። በአንድነት ወይም በኅብረት በምንሆንበት ጊዜ ደግሞ የበለጠ ኃይል ይኖረናል። ከዕብራውያን ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ፣ ከአዲስ ኪዳን ደግሞ ስለ ቤተ ክርስቲያንና የእግዚአብር መንግሥት ጠቃሚ ምሣሌዎች መመልከት ይቻላል። አንዳንዴ የእኛ የራሳችን ንብረት ይመስል ለሌሎች ኃይልን (ሥልጣንን) ስለማካፈል ወይም ለሌሎች ኃይልን ስለ መስጠት ስንናገር ይሰማል። ከዚህ ይልቅ ግን ሰዎች ኃይላቸውን ወይም ሥልጣናቸውን እንዴት ሊጠቀሙበት እንደሚገባ ማስተማሩና እኛም አብረናቸው መማሩ በጣም ይጠቅማል።

ብዙዎቻችን እንደምንስማማበት ኃይል እንዴት እንደምንጠቀምበት ከኃላፊነት ጋር የተያያዘ ነው። ኃይል ካለ፤ የዚያ ኃይል ምንጭ ማን ስለ መሆኑ፤ ያ ኃይል ሌሎች ላይ ስላሳደረው ተፅዕኖ ተጠያቂነትም ይኖራል።



አንድ ኃይል የሚመዘነው ተግባር ላይ ክምናውልበት ዓላማና ከውጤቱ አንጻር እንደሆነ ቀደም ሲል መመልከታችንን አትርሱ። እስቲ አሁን ደግሞ፣ እርስ በርስ በቅርበት የተያያዙ አምስት የኃይል ዓይነቶችን እንመልከት።

## አካላዊ ኃይል

አካላዊ ዓመፅን በመጠቀም ነገሮች እንዲፈጸሙ ወይም እንዳይፈጸሙ ማድረግ ይቻላል። የታጠቀ ዘራፊና የታጠቀ ፖሊስ በጣም የተለያዩ ቢሆኑም ሁለቱም የሚጠቀሙት አንድ ዓይነት መርሕን ነው- አናትህ ላይ መሣሪያ እስካነጣጠረ ድረስ መቃወም አትችልም የሚል። ሰፈር ውስጥ ሕፃናትን የሚያስቸግር ጉልበተኛ ና ዓለም አቀፍ ታዋቂነት ያለው ቦክሰኛ የሚጠቀሙት አንድ ዓይነት መርሕን ነው - በጉልበት ከአንተ እበልጣለሁ ስለዚህ የምልህን ሁሉ ማድረግ አለብህ የሚል። ምናልባትም ይህን ስለመሳሰሉ ነገሮች ማንበቡ ወይም መወያየቱ አንዳንዶቻችን ምቾት ይነሣን ይሆናል፤ ምናልባትም ሌሎች መነገር ያለባቸው ነገሮችም ሊኖሩ ይችላሉ። የፈለግነውን ወይም የምንወደውን ማግኘት ሲያቅተን (መልካምም ይሁን ክፉ) በጉልበት ለማግኘት እንፈልጋለን? ለዚህ የምናቀርበው አማራጭ መፍትሔ ምንድን ነው?

## ሀብት እንደ ኃይል

አንተ የምትፈልገው አንዳች ነገር ካለኝ በአንተ ላይ ኃይል አለኝ ማለት ነው። እንደ ፈለግሁት እንድትሆንልኝ ለማድረግ ባለኝ ሀብት ልጠቀምበት እችላለሁ። አንዳንዴ ወላጆች የልጆቻቸው መልካም ሥነ ምግባርን ለማበረታታት ይህን ዘዴ ይጠቀሙበታል፤ ጥሩ ልጆች ከሆኑ አንድ ነገር እንደሚሰጧቸው መጥፎ ልጆች ከሆኑ ግን ያንን እንደማይሰጧቸው ይነግሯቸዋል። ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማትም እንዲሁ መንግሥታትን በተመለከተ

በዚህ ዘዴ ይጠቀማሉ፤ እነርሱ የሚፈልጉትን ፖሊሲ ተግባር ላይ ቢያውሉ የገንዘብ ድጎማ እንደሚያደርጉላቸው፤ ያንን አሟልተው ካልተገኙ ግን ምንም ዓይነት እርዳታ እንደማይሰጧቸው ይነግሯቸዋል:: እዚህ ላይ ሀብት ሲባል ዕምቅ ተፈጥሮኣዊ ሀብትንም ያጠቃልላል:: ብዙዎች ሊጠቀሙበት የሚገባውን ሀብት ጥቂቶች ብቻ ተቆጣጥረውታል:: ታዲያ፤ ለእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የምናቀርበው አማራጭ መፍትሔ ምንድነው?

## ዕውቀት እንደ ኃይል

ይህ ከሀብት ጋር በጣም የተያያዘ ነው:: የምናውቀውን ወይም የተማርነውን ለራሳችን ጥቅም ብቻ ልናውለው እንችላለን:: እንደ ማንኛውም ነገር ሁሉ ዕውቀትም አንድ

ዓይነት ሀብት ስለሆነ ዓለም አቀፍ የባለቤትነተ ከለላ ይደረግለታል፤ እንደ ሸቀጥ ሁሉ ይገዛል ወይም ይሸጣል፤ ምናልባትም ያ ዕውቀት የማንም ሳሆን ሁሉ ባለ መብት የሆነበት ባላዊ ወይም የአገር ሀብት ሊሆን ይችላል:: ሌላው ዓይነት ኃይል ደግሞ የመገናኛ ብዙኃንን አጠቃቀም በተመለከተ ሊሆን ይችላል፤ የመገናኛ ብዙኃንን እውቀትን ለማካፈል ወይም ደግሞ እኛ የምንፈልገው ዓላማ እንዲያሟላልን ሐቁን አጣጥመን የምንጠቀምበት መገልገያ ልናደርገው እንችላለን::

## ሥልጣም እንደ ኃይል

አንዳንድ ሰዎች ኃይለኛ የሆኑት ካላቸው ሥልጣን ወይም ደረጃ የተነሳ ሊሆን ይችላል፤ ለምሳሌ ያህል ፕሬዚዳንቶችና ጠቅላይ ሚኒስትሮች፤ ጳጳሳትና ቀሳውስት፤ ዳይሬክተሮችና ሥራ አስኪያጆች፤ ባሎችና ወላጆች ደረጃቸውን እንደ አንድ አይነት የኃይል ምንጭ ሊጠቀሙበት ይችላሉ:: በአንዳንድ ሁኔታዎች ሥልጣን ወይም ደረጃ ኃይል የሚኖረው «በተገዢዎቹ» ስምምነት ብቻ ነው:: በአንዳንድ አገሮች ደግሞ ማኅበረሰቡ



ከሚሰጣቸው ክብር የተነሳ ሽማግሌዎች የተለየ ሥልጣን ይኖራቸዋል:: እነዚያ ባለ ሥልጣኖች በተሰጣቸው መብት በአግባቡና ኃላፊነት ባለው ሁኔታ እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ወይም የሚወስዱት እርምጃ የሌሎችን ፈቃደኛነት ያገናዘበ እንዲሆን ምን ማድረግ ይቻላል? እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ሌላው ጉዳይ ከመተዳደሪያ ደንባቸው ወይም በማኅበረሰቡ ውስጥ ካላቸው ድርሻ የተነሳ አንዳንዴ አብያተ ክርስቲያናትም ሥልጣንን መሠረት ያደረገ ኃይል ሊኖራቸው የሚችል መሆኑን ነው:: እዚህ ላይ ስለ መብት ያነሣነውን ጥያቄ ማቅረብ ይቻላል::

## ስብዕና እንደ ኃይል

አንዳንዶች ከሌሎች ላቅ ያለ ስብዕና ወይም ሞራላዊ ብርታት ሊኖራቸው ስለሚችል ትኩረታችን ሁሉ እነርሱ ላይ እንዲሆን፤ የሚነግሩንን ወይም የሚያደርጉትን ሁሉ አሜን ብለን እንድንቀበል ተፅእኖ ያሳድሩብናል:: ይህ ደግሞ ለበጎ የመዋሉን ያህል አንዳንዴ በተሳሳተ ዓላማ ሊጠቀሙበት ይችላሉ::

የኃይል ወይም የሥልጣን አጠቃቀምን በተመለከተ የተለያየ ተሞክሮ ሊኖረን ይችላል፤ አንዳንዶች ኃይላቸውን ለምን እንደሚያውሉትም ተመልክተናል:: ታዲያ፤ ያላቸውን ኃይል በአግባቡ ወይም በተሳሳተ መንገድ መጠቀማቸውን መመዘን የምንችለው እንዴት ነው?

## *የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት*

ንጉሥ ዳዊት በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ይታሰባል፤ አንደኛው በጀግንነቱ ሲሆን፤ ሁለተኛው የነበረውን ሥልጣን አግባብ በመጠቀሙ ነው:: ብዙዎቻችን እንደምናስበው የዳዊት፤ የቤርሳቤህና የኦርየን ታሪክ ልቅ ወሲባዊ ግንኙነት ላይ ብቻ የሚያተኩር አይደለም:: በዘመኑ በነበረው ባሕል ተቀባይነት ስለ ነበረው ዳዊት ከተለያዩ ሴቶች ጋር ግንኙነት ማድረጉ ይታወቃል:: ይሁን እንጂ ቤርሳቤህን ተመልክቶ ወደ ቤቱ ሲያስመጣት ዳዊት በአደገኛ መንገድ እየተጓዘ ነበር:: ቤርሳቤህ ፀነሰች:: ይህንንም ለመሸፈን ሲል ዳዊት ባልዋ ኦርዮን ከጦር ሜዳ መጥቶ ከሚስቱ ጋር መተኛትን አልፈለገም:: ስለዚህም ውጊያው በተፋፋመበት ግንባር እንዲሳተፍና እንዲሞት ዳዊት በሚስጢር ለባለ ሥልጣናቱ መልእክተኛ ሰደደ:: ኦርዮን በዐውደ ውጊያው ተገደለ:: ዳዊትም ከሚስቶቹ አንዷ እንድትሆን ቤርሳቤህን ወደ ቤቱ ወሰዳት::

**📖 2ኛ ሳሙኤል 12:1-7 አንብብ::**

ከታሪኩ እንደተመለከትነው ዳዊት በሥልጣኑ አለአግባብ የተጠቀመው እንዴት ነበር? ሥልጣኑን መከታ በማድረግ በደሉን ለመሸፈን ከፍተኛ ሙከራ አድርጎ ነበር፤ ይሁን እንጂ ናታን ካቀረበው ታሪክ መመልከት እንደሚቻለው በሥልጣኑ አለ አግባብ የመጠቀም ፍላጎቱን መቆጣጠር አለመቻሉን የሚያሳየው ምን ነበር?

**📖 ፊልጵስዩስ 2:5-11 አንብብ**

ይህ በጣም ውብ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ሲሆን ምናልባትም ጳውሎስ ቀደም ሲል ከነበረ የምሥጋና



መዝሙር የጠቀሰው ሳይሆን እንደማይቀር ይታሰባል:: ክርስቶስን በተመለከተ ብዙ ልናሰላስለው የሚገባ ቁም ነገር አለው:: ይሁን እንጂ እዚህ ላይ የምናተኩረው ኃይልን ወይም ሥልጣንን አስመልክቶ የሚናገረው ላይ ብቻ ይሆናል::

ኃይልን ወይም ሥልጣንን መጠቀምን በተመለከተ ምንባቡ ምን ይላል?

ራሱን ባዶ ማድረጉ፤ የሰዎችን ደካማ ሥጋ መልበሱና ሞቱ ኃያል ወይም ውጤታማ የሆነው ለምንድን ነው?

ከሌሎች ጋር ባለህ ግንኙነት ኃይልን ወይም ሥልጣንን መጠቀምን በተመለከተ ከእነዚህ ሁለት ምንባቦች ያገኘ ኸው ትምህርት ምንድን ነው?

# የፍትሕና የጽድቅ ሕይወትን መኖር የሚቻለው እንዴት ነው?

## *መንደርደሪያ*

«እንዲህ መሆኑ ፍትሐዊ አይደለም» ወይም «ይህ በፍጹም ትክክል አይደለም» በማለት የተናገርክበትን ጊዜ አስብ:: እንዲህ በማለት የተናገርከው አንተ ላይ ወይም ሌሎች ላይ የደረሰውን በደል ምክንያት በማድረግ ሊሆን ይችላል:: ለመሆኑ፤ ፍትሐዊ አይደለም ወይም ትክክል ይደለም ያሰኘህ ምን ኖሯል? ወደዚህ መደምደሚያ የደረስከው እንዴት ነበር? አንገም ሆንህ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሌሎች በሁኔታው ምን ተሰማችሁ?

ባለህበት አካባቢ፤ በሀገርና በዓም አቀፍ ደረጃ ሰዎች እየተነጋገሩ ያሉት ምን ዓይነት ዜና ነው? ከእነዚህ መካከል ፍትሕ መጓደሉን የሚያመለክቱ የትኞቹ ናቸው? ፍት መጓደሉን የሚያመለክቱ አንዳንድ ነገሮች ከሌሎቹ ይልቅ ይበልጥ ስሜታችንን የሚነኩት ለምንድን ነው?

## *ፍትሕን በተመለከተ በጥልቀት ለማሰብ እንዲረዳህ*

ስለ ፍትሕ ስናስብ ቶሎ ወደ አእምሮአችን የሚመጡት የፍርድ ቤት ችሎት፤ ዳኞች፤ ጠበቆች፤ ከሳሾችና ምስክሮች ናቸው:: በፍርድ ቤት አካባቢ ፍትሕ መኖሩ በጣም አስፈላጊ ቢሆንም፤ ስለ ፍትሕ ስንናገር ግን በዚያ ብቻ መወሰን እንደሌለበት ግልጽ ሊሆንልን ይገባል::

ፍትሕ፤ ፍርድ ነክ ጉዳይ ብቻ አይደለም፤ ፍትሕ፤ ሞራላዊና ሥነ ምግባራዊም ጭምር ነው::



ፍትሕ ስንል መልካም ግንኙነት ይኖር ዘንድ መልካም ማድረግንም ይመለከታል:: «መልካም» ወይም «ትክክል» ሲባል ምን ማለት እንደ ሆነ ለውይይት መቅረብ ያለበት ጉዳይ ቢሆንም፤ ሌሎችን በደለኛ ከማድረግና ፍርድን ከማስተላፍ በላይ ርቀን መሄድ ይኖርብናል::

ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን እግዚአብሔርን በሁለት የተለያዩ ገጽታዎች ያቀርቡልናል:: አንደኛው ስለ እግዚአብሔር የሚሰጠን ምስል ፍርድ የሚያስተላልፍ ዳኛ ዓይነት ነው:: ሌላው ግን ስለ እግዚብሔር የሚሰጠን ምስል ፍትሕ አድራጊና ፍትሕ እንዲፈጸም የሚያደርገው እርሱ መሆኑን ነው:: የመጀመሪያው፤ የእግዚብሔር ድርሻ መልካምና ክፉን በተመለከተ የመጨረሻውን ውሳኔ የሚሰጠው እርሱ መሆኑን ያቀርብልናል:: በዓለሙ እየተደረገ ያለውን ነገር እግዚብሔር ገለልተኛ ሆኖ አይመለከትም፤ ይልቁንም አንዳችን ሌላው ላይ በምንፈጽመው ሁሉ ተጠያቂ ያደርገናል:: ሁለተኛው ግን፤ መልካም ግንኙነት ይኖር ዘንድ አሁኑኑ እርምጃ ይወሰዱ ዘንድ ሰዎችን ያነሣሣል እንጂ ፍትሕ አሸንፎ እንዲወጣ እግዚብሔር የግድ የመጨረሻው የፍርድ ቀንን እንደማይጠብቅ ያቀርብልናል:: ምህረትና ፍትሕ በፍጹም የማይነጣጠሉና አብረው የሚሄዱ ነገሮች ናቸው የሚባለው በዚህ ምክንያት ነው፡ ዋናው ዓላማው ለሌላው መቀጣጫ እንዲሆን የበደለውን ወገን መቅጣት አይደለም:: ይልቁንም መጀመሪያውኑ አዲስና መልካም ሥርዓትን ማስፈን ነው::

ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንዱ «መጽሐፈ መሳፍንት» በመባል ይታወቃል፤ መሳፍንት የሚለውን የአማርኛ ቃል እንግሊዝኛው "Judges" ይለዋል:: ይህም «ዳኞች» ወይም «ፈራጆች» ማለት ነው:: መጽሐፉ የተበላሸውን እንዲያስተካክሉ፤ ለተበደለው በጽድቅና በፍትህ

እንዲዳኙለት እግዚአብሔር ያስነሳቸውን ወንዶችና ሴቶችን ታሪክ ይዞአል:: ከእኛ እይታ አንጻር በመነሣት ስለ ነበራቸው ዓላማና ይወስዱት ስለ ነበረው እርምጃ ጥያቄዎች ሊኖሩን ቢችሉም የእነዚህ ሰዎች ዋናው ሥራ ፍትሕን ማስፈን ነበርለለ የነቢያቱም ተልዕኮ እንዲሁ ፍትሕን የሚያመለክት ነበር:: የፍትሕ መስፈንን በተመለከተ እግዚአብሔር ለሚያቀርበው ጥሪ በዘመናት የተነሱ ሰዎች የየራሳቸውን ምላሽ ሲሰጡ ኖረዋል:: ዛሬም ለእኔና ለእናንተ ተመሳሳይ ጥሪ ቀርቦልናል::

የፍትሕ መጓደል አንድ ዓይነት ዐመጽ ነው:: የተዛነፈውን ለማስተካል፤ የተጓደለውን ለሟሟላት ሰዎች በኃይል እንዲጠቀሙ ሊያነሳሳቸውም ይችላል:: የፍትሕ መጓደል ፖለቲካ፤ ዘርን ወይም ብሔርን መሠረት ያደረገ ዐመፅ እንዲቀሰቀስ ያበረታታል:: በዚህ ዓለም የመኖር መብታቸውን ለማስከበር የሚነሳሱ ወገኖች የሚፈጽሙት ጭካኔ ያስደነግጠን ይሆናል:: ይሁን እንጂ ይህ ዓይነቱን እርምጃ ለመውሰድ ምክንያት የሆናቸው ምን ዓይነት የፍትሕ መጓደል ቢፈጸምባቸው ነው ብለን መጠየቃችን የማይቀር ነው:: ያም ሆነ ይህ ፍትሕ በተጓደለበት መልኩ ምንም ዓይነት የተረጋጋ አኗኗር ሊመሠረት እንደማይችል ግልጽ ነው::

ፍትሕና ሰላም ስላላቸው ተያያዥነት ስናስብ በመጀመሪያ ደረጃ «ሰላም» የሚለውን ቃል ስለምንጠቀምባቸው የተለያዩ መንገዶች መረዳት ይጠቅማል:: ጦርነት ወይም ጸብ ሲያበቃ ለጊዜውም ቢሆን ሰላም ወርዶአል እንላለን:: ይሁን እንጂ ዘላቂ ሰላም ሊኖር የሚችለው የፍትሕ መጓደል ሲስተካከልና እውነተኛ ዕርቅ ሲኖር ብቻ ነው:: ሰላም እንዲኖር ከተፈለገ ለዐመፅ ምክንያት የሆኑ ነገሮችም እልባት ማግኘት አለባቸው:: በሌላ በኩል ደግሞ ፍትሕን ለማስገኘት



የምንጠቀምባቸው አንዳንድ መንገዶች ለምሳሌ ያህል በሰው ዘር ላይ ወንጀል የፈጸሙ ሰዎችን ለፍርድ ማቅረብን የመሳሰሉ አሠራሮች ዓመፃን ሊያነሳሱ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል::

አንድ ነገር የፍትሕ ጉዳይ የሚሆነው ከሰዎችም ሆነ ከእግዚአብሔር ሕግጋት አንጻር ትክክል ወይም ስሕተት ሲሆን ነው፤ ወይስ መልካም ግንኙነትና ሕብረት መፍጠር ሲችል? ለዚህ ጥያቄ የምንሰጠው መልስ በምንወስደው እርምጃ ላይ የሚያመጣው ልዩነት ምን ሲሆን እንደሚችል ታስባለህ?

የፍትሕ መጓደልን የሚያመለክቱ የተለያዩ ነገሮችን መጥቀስ ይቻላል:: ይሁን እንጂ አሁን የምንመለከተው አራቱን ብቻ ይሆናል:: አራቱም የሰዎችን የመኖር መብት ይጋፋሉ፤ ለዓመፅ መኖር ምቹ ሁኔታንም ይፈጥራሉ::

### ኤኮኖሚያዊ ፍትሕ አልባነት

በአገር አቀፍም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተስተካከለ የሀብት ክፍፍል አለመኖሩ ይታወቃል:: አንድ ክልል ወይም አገር በተፈጥሮ ጸጋ የታደለ ቢሆንም፤ አብዛኞቹ ዜጎች ግን በድህነት ሊኖሩ ይችላሉ:: አንዳንዶቹም ራሳቸውን መርዳት የሚችሉበት አማራጭ በማጣታቸው ተመጣጣኝ ባልሆነ ክፍያ ችሎታቸውን ወይም ዕውቀታቸውን ያስበዘብዛሉ:: በብዙኀኑ ኪሣራ ጥቂቶቹ ሲበለጽጉ ደግሞ ደጋግሞ በታሪክ የታየ እውነት ነው:: ግሎባላይዜሽንን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ የኤኮነሚ ሥርዓቶች ይህን ፍትሕ አልባነት በዓለም አቀፍ ደረጃ አስፋፍተውታል::

### ፖለቲካዊና ማኀበራዊ ፍት መጓደል

ብዙዎቻችን በተለያዩ የውክልና ዲሞክራሲዎች ከፍተኛ እምነት አለን፤ እንዲህ ያሉ ሥርዓቶች ቢዘረጉ ኖሮ ሰዎች በፍቅርና በሰላም መኖር ይችሉ እንደ ነበር

እናስባለን። ይሁን እንጂ የቱንም ያህል ኃይል ቢጠቀሙም በጣም ጠንካራ የተባሉ መንግሥታት እንኳ የተረጋጋ ሕይወት እንደሌላቸው ግልጽ ነው። ብሔራዊ ሰላምን ወይም ዋስትናን ማስከበር በሚል ሽፋን የብዙዎች ፖለቲካዊና ማሕበራዊ መብት ይታፈናል። በአንዳንድ ክልሎች ወይም በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ ባለሥልጣኖች ኃላፊነት የማይሰማቸውና ጨርሶም እነርሱን የማይወክሉ መሆናቸውን በመረዳታቸው ይወክሉናል ወይም ይሰሩልናል ብለው ማንንም እንደማይመርጡ ይታወቃል። ብዙ ጊዜ ደግሞ ፍትሕ ወደ ሃብታሞቹና ወደ ጉልበተኞቹ ሲያጋድል ይታያል። ሌላው ቀርቶ ሕግን የማስከበር ረጅም ዘመን ታሪክ ባላቸው አገሮች እንኳ ሰዎች ተደማጭነትን በገንዘብ ይገዙታል፤ የፖለቲካ ሥልጣን ስላላቸው ብቻ ብርቱዎች በክፉ ሥራቸው ተጠያቂ አይሆኑም።

## ባሕላዊ ፍትሕ መጓደል

ኢምፔሪያሊስቶችና ቅኝ ገዢዎች ኃይልን በመጠቀም በሌሎች ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ማንነት ጫና ያደርጋሉ። ብዙውን ጊዜ ደግሞ ይህን ዓላማቸውን እውን የሚያደርጉት መገናኛ ብዙኃንን በረቀቀ ዘዴ በመጠቀም ነው። የአገሬው ሕዝብ ባሕል የቱንም ያህል ጠቃሚ ቢሆንም፤ እንዲወገድ ይደረግና በምትኩ የራሳቸው ያልሆነ ባሕልን እንዲቀበሉ ተፅዕኖ ይደረግባቸዋለው። ብዙ ጊዜ ደግሞ ከውጪ የመጣው ባሕል የሚስፋፋው ግለኝነትን፤ የኢኮኖሚ መሳካትን፤ ወንጀልና ዓመፅን በማሞገስ ነው።

## ዘርን ወይም ጎሳን ተገን ያደረገ የፍትሕ መጓደል

ዘርን ወይም ጎሳን ተገን የሚያደርግ የፍትሕ መጓደል በመልካቸው ወይም በቁመናቸው ብቻ ሌሎችን ይንቃል፤ አንዱ ዘር ወይም አንዱ ሕዝብ ከሌላው የበለጠ እንደሆነ ያስባል። ባለፉት ዓመታት ጥቁሮች በሰብዓዊነታቸው ከሌሎች ያነሱ እንደሆነ ይታሰብ ነበር፤



ከዚህም የተነሳ ገዢዎቻቸው ከፍተኛ ውርደትና ጭቆና ያደርሱባቸው ነበር።

ቀደም ሲል እንዳልነው እነዚህ ነገሮች የሰዎችን ክብር ይነካሉ፤ ውጤታማው መንገድ ያ ብቻ የሚመስላቸው ወገኖችንም ለዓመፅ ሊያነሳሱ ይችላሉ። እንዲህ ያለ የፍትሕ መጉደልን ወደ ትክክለኛ ግንኙነት ለመለወጥ እንዴት መሥራት አለብን? ፍትሕ ማስፈን የሚቻለው እንዴት ነው?

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ከታሪክ በተደጋጋሚ እንደታየው ሌሎችን መበዝበዝ ከሰው ልጆች ባሕርይ ጋር የተያያዘ ይመስላል:: ከእግዚብሔር በታች እስከ ሆኑ ድረስ እስራኤላውያን እርስ በርስ ተከባብረው መኖር ችለው ነበር:: ይሁን እንጂ ፍትሕ ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ የእግዚብሔር ነቢያት በየጊዜው ማሳሰባቸውን አላቋረጡም::

🕮 አሞጽ 8:4-7 አንብብ

የምንሸጠው ጥራጥሬ ቢሆን ወይም የኮምፒዩተር መለዋወጫ ዕቃዎች ዋጋ እስካጭበረበርን ድረስ ያው ወንጀል ከመሆን አያልፍም::: በዚህ መሐል በጣም የሚጎዱት ደግሞ ድሆች ናቸው:: ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸውን ወይም ጥራት የጎደላቸውን ነገሮች ምርጥና ተፈላጊ ናቸው ብሎ ለገበያ ማቅረብ ወንጀል ነው:: በተለይ ደግሞ ይህን የሚያደረርጉት ሃይማኖተኞች ከሆኑ ግብዝነታቸውን ከማጋለጡም በላይ ጥፋቱን እጥፍ ድርብ ያደርገዋል፤ እንዲህ ያሉ ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀምጠው አእምሮአቸው ግን እንዴት አድርገው ሌሎችን እንደሚያታልሉ ያውጠነጥናል::

ፍትሕና አምልኮ መነጣጠል የሌላቸው ጉዳዮች ናቸው የሚባለው እንዴት ነው?

ከነብዩ አሞጽ 800 ዓመታት በኋላ የመጣው ኢየሱስ ናዝሬት በነበረው ምኩራብ ውስጥ ለአገልግሎት መሠረት የሚሆነውን ክፍል ከኢሳይያስ መጽሐፍ አነበበ::

🕮 ሉቃስ 4:17-21 አንብብ

ሉቃስ እንደሚናገረን ይህ ታሪክ የተፈጸመው ኢየሱስ በምድረ በዳ ከተፈተነ በኋላ ነበር:: ኢየሱስ በሥጋዊ ዓይን ሲታይ የሚጠቅም ወይም ለአገልግሎቱ መስፋፋት



ሲታይ የሚጠቅም ወይም ለአገልግሎቱ መስፋፋት ምክንያት ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚታሰብ እርምጃ እንዲወስድ ተፈትኖ ነበር፤ እርሱ ግን ፈተናውን ተቋቁሞ አሸንፎአል:: ለድህነት፤ ለምርኮ፤ ለዕውርነትና ለጭቆና ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ከማውገዝ ወይም ካሣ እንዲከፍሉ ከመጠየቅ ይልቅ ኢየሱስ የተናገረው ለተፈጠው ችግር ዘላቂ መፍትሔ የሚሆን ነበር:: ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ እውነተኛ ፍትሕ ሲሰፍን ብቻ ነው::

የእኛን ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ የሚመለከቱ ሰዎች እንዲህ ያሉ ቃላትን የሚናገሩልን ይመስልሃል?

ፍትሕን በማስፈን ረገድ እነዚህ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች የሚያስተላልፉልን መልእክት ምንድን ነው?

# ምን ዓይነት ማንነት?

## መንደርደሪያ

ስለ ማንነቴ ይናገራሉ ብለህ የምታስባቸውን አንዳንድ ነገሮችን ሰበስብ:: ለምሳሌ ያህል፤ የልደት ሰርቲፊኬትህ፤ ፓስፖርትህ ወይም መንጃ ፈቃድህ ስለ አንተ የሚናገሩት ይኖራቸዋል:: ከሌሎች ጋር ስላለህ ግንኙነት፤ ስለ እምነትህ፤ ስለምታድርጋቸው ነገሮች፤ ስለምትወዳቸው ነገሮችና ስለ ስብዕናህ ይናገራሉ ብለህ የምታስባቸው ነገሮች ምንድናቸው?

(በቡድን የምታጠኑ ከሆነ ብቻ) እያንዳንዱ ሰው ስለ ማንነቴ ይናገራሉ ብሎ የሚያስባቸው አሥር ነገሮችን ይጻፍ:: እነዚህን ዝርዝሮች ሰብስቡና እጃችሁ እንዳመጣ በስፍራው ላሉ ሰዎች አከፋፍሉቸው:: እያንዳንዱ ሰው አስፈላጊ ከሆነም ከሌሎች የቡድኑ አባሎች ጋር በመሆን ዝርዝሮቹ ስለ ማን እንደሚናገሩ ለማወቅ ይሞክር::

## ማንነትን በተመለከተ ለማሰብ እንዲረዳህ

እኛ ራሳችንን በምናይበት መንገድ ሌሎች እንደማያዩን ስንረዳ ምናልባት እንገረም ይሆናል:: ይህም መረዳት አስፈላጊ መሆኑን ለማሳየት ሁለት ምክንያቶችን ማቅረብ ይቻላል:: በመጀመሪያ ደረጃ ሌሎች እኛን የሚያዩን እኛ ራሳችንን በምናይበት ሁኔታ አለመሆኑን ስንረዳ ምናልባት ከእነርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት ሊያሻክረው ይችላል:: በሁለተኛ ደረጃ፤ አንዳንዴ መሆን በምንፈልገውና አሁን ባለው ትክክለኛ ማንነታችን መካከል ያለውን ልዩነት ጠንቅቀን እንደማናውቅ ግልጽ ይሆንልናል:: ቀለል ያለ ምሳሌ ለማቅረብ ያህል፤ አንድ



ቤተ ክርስቲያን እንግዶችን የምትቀበልና ወደዚያ የሚመጡትን ሁሉ እንኳን ደኅና መጣችሁ የምትል እንደሆነች ታስብ ይሆናል:: ወደዚያ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡና እንኳን ደህና መጣችሁ የሚላቸውን ያላገኙ ሰዎች ግን ለዚያች ቤተ ክርስቲያን ያላቸው አመለካከት በተቃራኒው ሊሆን ይችላል::

መልካም ግንኙነትን መመሥረት እንድንችል ከተፈለገ፤ ራሳችንን በትክክለኛው መንገድ ማየትና በሌሎች ዘንድ ስላለን ግምት ማሰብ ይኖርብናል:: ይህን የምናደርገው ደግሞ ምንም ሳንሸፋፍንና ድካማችንን ለመቀበል በተዘጋጀ ልብ መሆን አለበት:: በጨቋኝና ግፈኛ ሥርዓት ውስጥ የቱንም ያህል በደል ቢደርስብን እውነተኛ ማንነታችንን እንዳንጥል መጠንቀቅ ይኖርብናል:: ቤተ ክርስቲያን የእግዚብሔር መንግሥት ተስፋን ትወክላለች:: በእንቅስቃሴዋ የእግዚብሔር መንግሥት ነጸብራቅ የማይታይ ከሆነ ግን ማንነቷ ጥላለች ማለት ነው:: ቤተ ክርስቲያን ትክክለኛ ማንነቷን ጠብቃ ከተንቀሳቀሰች ግን አምልኮችን በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ከመታየቱም በላይ ሰፊና ሌሎችንም የሚያቅፍ እንዲሆን ያስችለዋል::

ብዙውን ጊዜ በማኅበረሰቡም ሆነ በአገር ደረጃ በሚፈጠር ችግር ሃይማኖተኞቹ ለራሳቸው የሚሰጡት ማንነትና ሌሎች የሚሰጡአቸውን ማንነት ማለታችን ነው:: በመሠረቱ የችግሩ ይዘትም ሆነ ሃይማኖታዊነት በጣም የተወሳሰቡ ነገሮች ናቸው:: ሃይማኖት የችግሩ ምክንያት ነው ከማለት ይልቅ ለችግሩ ለራሱ ድርሻ ሊኖረው ይችላል ማለቱ የተሻለ የሚሆነው በዚህ ምክንያት ነው:: በጣም ተቀራርበው በሚኖሩ ማኅበረሰቦች መካከል ለዓመፅ ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮች ከሥራ፤ ከቤት ኪራይ፤ ከትምህርት፤ ከጡረታ መብት፤ ከዘር በየጊዜው

ከሚወጡ ፖሊሲዎችና ከመሳሰሉት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ሊሆኑ ይችላሉ። ምንም እንኳ ችግሩ ከላይ ከተጠቀሱት አንዱ ብቻ ቢሆንም፤ ኃይማኖታዊ ልዩነት በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ውጥረት በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ሊኖረው ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ በመካከላቸው ግጭት ያለባቸው ብድኖች በተለያየ መጠሪያ ቢታወቁም፤ የአለመግባባታቸው ምክንያት ተመሳሳይ እስከሆነ ድረስ የሚያመጣው ልዩነት አይኖርም። ይሁን እንጂ ሐቁ ማንነትን ለመግለጥ የሚጠቀሙት በሃይማኖት አማካይነት መሆኑ ነው። በክርስቲያችና በእስላሞች፤ በክርስቲያኖችና በአይሁዶች፤ በእስላሞችና በአይሁዳች፤ በሒንዱዎችና በሲኪዎች መካከል የተለያዩ ግጭቶች ተፈጥረዋል፤ ብዙ ኅብረቶችም ተደርገዋል። በየጊዜው የሚነሱ ግጭቶችን «ይኸኛው ክርስትናን የሚመለከት አይደለም» ብለው የሚያስቡ ሰዎች ችግሩ ክርስቲያነችንም ማሳተፍ ያለበት ነው ብለው ከሚያምኑት ጋር ግጭት መፍጠራቸው የማይቀር ነው።

በመሠረታዊ ደረጃ፤ ሙሉ ለሙሉ ሃይማኖታዊ የሆነ ማንነት ይኖራል ወይ? በማለት እንጠይቅ ይሆናል። ሃይማኖታዊ ማንነት ዋናው ተያያዥነቱ ከእምነታችን ጋር ነው፤ ያም ሆኖ ግን በዚያ ብቻ አይወሰንም። ክርስቲያኖች ሁሉ የጋራ በሆኑ እምነቶች ይስማማሉ፤ ለምሳሌ ያህል የሐዋርያት የእምነት መግጫን ማቅረብ ይቻላል። እንዲህ ማለት ግን የእነርሱ ወገን የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የጋራ የሆነ ማንነት አላቸው ማለት አይደለም። ሐቁ ከዚህ በጣም የራቀ ነው።

አንድ ዓይነት አቋምን በተመለከተ የጋራ የሆነ ማንነት ሊኖር የሚችለው እስከ ምን ድረስ ነው? ወይም ደግሞ ማንነት በየጊዜው እያደገና እየዳበረ የሚሄድ ነገር አይደለም ወይ? የሚለው አስተሳሰብ አብያተ ክርስቲያናቱን



ሊያከራክራቸው ይችላል። እንግዲህ ሃይማኖታዊ ማንነታችን ከብሔራዊ፤ ከዘርና ከፖለቲካ ማንነታችን ይለየናል የምንል ከሆነ ወይም ደግሞ ከዘመዶቻችን ወይም በምንሠራው ሥራ ካገኘነው ማንነት ይለየናል የምንል ከሆነ እምነታችን ሁለንተናችንን መግለጽ በሚችል መልኩ እየተጠቀምንበት አይደለም ማለት ነው።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ብዙውን ጊዜ ማንነታችን የሚገነባው በማኅበረሰቡ ውስጥ ነው። ምክንያቱም በከፊልም ቢሆን ማንነታችን የሚመጣው ከሌሎች ጋር ባለን ዝምድና ወይም ቀረቤታ ነው። የምንናገረው ስለ ሃይማኖታዊ ማንነታችን ከሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ስላለን ግንኙነት እየተነጋገርን ነው ማለት ነው። በዚህ የጥናት መመሪያ ቀደም ብለን በተመለከትነው ክፍል ዓመፅን፤ ኃይልና ፍትሕን በምንረዳበትና እግዚብሔርን በምንረዳበት መንገድ መካከል ጥብቅ ግንኙነት መኖሩን አይተናል። በክርስቶስ ከእግዚብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ማንነታችንን ከመገንባት ይልቅ፤ እኛን በመሰለንና ደስ ባሰኘን ጉዳይ ዙሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኘ -ነት ለመመሥረት እንሞክራለን።

ማንነታችን በትክክለኛ መሠረት ላይ እንዲገነባ ከተፈለገ ማን እንደሆንንና ከሌሎች ጋር የምንያያዘው እንዴት እንደሆነ ለመመርመር ጊዜ ሊኖርን ይገባል። የተለያየ አቋምና አመለካከት ያላቸው ወገኖችን እርስ በርስ ለማቀራረብ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ በአንድ ወቅት ውይይት አዘጋጅቶ ነበር። በዚያ ውይይት የተሳተፉ ሁሉ ራሳቸውን ሆነው ለመገኘት ፍጹም ነጻነት ነበራቸው። እንዲህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ሰዎችን መጠቀሚያ ለማድረግ ሳይሆን ባሉበት ሁኔታ ስናከብራቸውና ማንነታቸውን ስንቀበል ብቻ ነው።

በሃይማኖቶች መካከል እርስ በርስ መግባባትና

መቀራረብ ሊኖር ይገባል ስንል አንዳንዶች «ይኼማ ገደቡን ማለፍ ነው» ይሉናል። እምነታችንን ወይም አቋማችንን የማይጋሩ ሰዎችን አለመቀበል የማንነታችን ዋነኛ ክፍል እንደሆነ እናስብ ይሆናል። ወገናዊነትና አክራሪነት ሊኖር የቻለው ከሌላኛው ወገን ለሚቃጣው ልዩነትን የማጠንከር ዝንባሌ ምላሽ ለመስጠት መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ደግሞ ወደ ጭፍንነትና ማንነት ለተሳሳተ ዓላማ ወደ ማዋል ያመራል።

ስለ ሌሎች ያለን ቀና አመለካከት ለሚስዮናዊ ሥነ መለኮት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ከዚያ ውጪ ተግባር ላይ የምናውለው ሚስዮናዊ እንቅስቃሴ ግን የሌሎችን ክብር ከመዳፈር ያለፈ ሆኖ አይታይም። ብዙውን ጊዜ ክርስቲያን ሚስዮናውያን የሚያገለግሉአቸው ሕዝቦችን ባሕል ለማክበር ጠንቃቆች አልነበሩም፤ ወንጌልን በተቀበሉ ሁሉ ላይ ምዕራባዊ ማንነት ይጭኑባቸዋል። ይህን በደል በተመለከተ ሁላችንም ንስሐ ብናደርግ በተለያየ የዓለማችን ክፍል ባሉ ክርስቲያኖች መካከል ቀና ግንኙነት ሊኖር ይችላል።

ከመልካም ሰብዓዊ ቀረቤታ የተነሳ ሰዎችን በመቀበልና የሚያምኑትንም በመቀበል መካከል ልዩነት ሊኖር ይችላል? ለያዝነው አቋም በጣም የተሰጠን ልንሆን እንችላለን። ይህን ግን ለሌሎች ግልጽ ከመሆን ጋር እንዴት ማስታረቅ ይቻላል? ከእኛ የተለየ እምነት
ቢኖራቸውም ይህን ልዩነት እንደ አደጋ ሳይሆን እንደ አንድ እምነታችንን ማበልጸግ እንደሚችል ጉዳይ ማየት የሚቻለው እንዴት ነው?



# *የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት*

በእግዚአብሔር የተመረጠ ሕዝብ መሆን መብትም ኃላፊነትም ነው። ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ ጉባዔ ይህን በግልጽ ተናግሮ ነበር።

📖 **ዘዳግም 10:12-22 አንብብ**

ከመብት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሁለት ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ - አንዳንዴ ትኩረታችን ሁሉ መብታችን ላይ ይሆንና ኃላፊነታችንን እንዘነጋለን። ወይም ደግሞ መብት የምንለውን በተወሰኑ ሰዎች ብቻ እንገድበዋለን። ከአይሁዳውያን ቅዱሳት መጻሕፍትም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እነዚህ ችግሮችን አስመልክቶ ብዙ ምሳሌዎችን ማቅረብ ይቻላል። ምናልባትም ሙሴ መብትና ኃላፊነት የማይነጣጠሉ መሆናቸውን አጠንክሮ የተናገረው በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም፤ ከእነርሱ በኋላ የተነሱ ነቢያትም የእርሱን ምሳሌ ተከትለዋል። «ከእግዚአብሔር ሽልማትን እንድትቀበል ሕጎቹን መጠበቅ ይኖርብሃል» የሚለውን ብቻ ከማስተማር ይልቅ በሁለቱም መካከል ሕያው ግንኙነትና ኅብረት ይኖራል።

ምንም እንኳ፤ እስራኤላውያን የተለየ መብትና ኃላፊነት ቢኖራቸውም፤ ይህ መብትና ኃላፊነት የተለየ ባሕል ያላቸውን፤ ሙሉ በሙሉ በትውልድ አይሁዳዊ ያልሆኑ ከእነርሱ ጋር ለመኖር የመጡ ሕዝቦችንም ያጠቃልላል። እግዚአብሔር ለደካሞችና በማኅበረሰቡ ውስጥ ምንም ዓይነት ሥልጣን ለሌላቸው ሰዎች እንዲጠነቀቅ አሳይቶአል።

በቤተ ክርስቲያን ያለን መብትና ኃላፊነት በማኅበረሰባችን ውስጥ ያሉ እንግዶችንም ያጠቃልላል ወይም ያገለግላል? ለእኛ ለምናምነው እንደሚጠነቀቅ ሁሉ እግዚአብሔር ለእነርሱም ይጠነቀቃለ ሲባል ምን ማለት ነው?

📖 **ኤፌሶን 2:12-18 አንብብ**

እዚህ ላይ ጳውሎስ እየተናገር ያለው ክርስቶስ በሰዎች መካከል ያለውን እንዲያውም በክርስቲያኖችና በአይሁዶች መካከል ያለውን ልዩነት ማፍረሱን ብቻ አይደለም። እንደዚያ ቢሆን ኖሮ በራሱ ትልቅ የምሥራች ይሆን ነበር። ራቅ ብሎ በመሄድ የኤፌሶን መልእክት የሚነግረን አዲስ ሰውን በመፍጠር ክርስቶስ ሥር ነቀል ለውጥ ማድረጉን ጭምር ነው።

ቤተ ክርስቲያናችንና ማኅበረሰባችንን በሚለያይ የጥል ግድግዳ ተገድበን ሳይሆን በክርስቶስ ባለን አዲስ ሰውነት ትክክለኛ ስፍራችንን የምንይዘው እንዴት ነው?



## *ምን ማድረግ ይኖርብናል?*

በዚህ ጥናት መመሪያ የተመለከትናቸው ርዕስ ጉዳዮች ረጅሙን ጉዞ ለማድረግ የመጀመሪያ እርምጃዎች ናቸው ማለት ይቻላል። እስከ አሁን የተነጋገርንባቸው ጉዳዮች ዕይታህን እንዳሰፋና ተጨማሪ ጥያቄዎችን እንድታነሳ ምክንያት ሳይሆንህ እንዳልቀረ ተስፋ እናደርጋን። ክርስትና እምነታችን ከምንገምተው በላይ ብርቱ መሆኑን በመገንዘብ ነገሮች፤ አሁን ባሉበት ሁኔታ ረክተህ እንድትቀመጥ እንደማያደርግህ እርግጠኞች ነን። ራሳችንን፤ አብያተ ክርስቲያኖቻችንንና ማኅበረሰባችንን ለመለወጥ እኛ የምናደርገው ይኖራልን?

## *ዕይታን ማስፋትና በጥልቀት መመልከት*

ዓመፃን ማስወገድና ዕርቅና ሰላም ማስፈንን የመሰለ በጣም ሰፊ ጉዳይ በዚህች ትንሽ ጽሑፍ ብቻ ማካተት እንደማያቻል እንረዳለን። ያም ሆኖ ግን ውጤት ያለው እርምጃ እንድንወስድ ከተፈለገ ትኩረታችንን ወደ አንድ አቅጣጫ ማነጣጠር ይኖርብናል። በጣም አስፈላጊ ናቸው የምትሏቸው አንድ ወይም ሁለት ርዕስ ጉዳዮችን ለይታችሁ ማውጣት ሞክሩ። ምናልባትም እነዚህ ችግሮች በአካባቢያችሁ ብቻ የተወሰኑ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ወይም ዓለም አቀፍ ይዘት ያላቸው ሰፋ ያሉ ጉዳዮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፤ ለምሳሌ ያህል አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች በማኅበረሰባቸው ውስጥ ያለ የመንገድ ላይ ወንጀልን በተመለከተ መፍትሔ ለማምጣት ይንቀሳቀሱ። ሌሎች ደግሞ የድሀ አገሮች ዕደ እንዲሰረዝ በዓለም አቀፍ ደረጃ ድምፃቸውን ያሰማሉ። የምንሳተፈው በየትኛው ዓይነት እንቅስቃሴ ቢሆንም ሁኔታዎችን በጥልቀት እንመልከት፤ መሠረታዊ ችግሮችን እናመዛዝን፤ ከዚያ በኋላ የሌላ አገር ሰዎችን ተሞክሮ ግምት ውስጥ በማስገባት እንማር።

## ማድረግ የምንፈልገውን እንወቅ

ዓመፃን ማሸነፍ መቻል አለብን:: ለምሳሌ ያህል በሕፃናት ላይ የሚፈጸም ወንጀል ወይም በጎሳዎች መካከል የሚደረግ ግጭት እንዲቆም መናገሩ ብቻ በቂ አይደለም፡፤ ብዙውን ጊዜ ዓመፅ ከዚያ በፊት የነበሩ ሥር የሰደዱ ችግሮችን መሠረት ያደርገ ነው:: ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ማስወገድ የሚቻልበትን መንገድ በጥልቀት እናስብ:: ከዚያ በኋላ ደግሞ ለዓመፃ ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎችን መጠን ዝቅ ለማድረግ ወይም ጨርሶ ለማጥፋት እንቅስቃሴ እናድርግ:: ዓመፃን በተመለከተ መፍትሔ የሚሆኑ ቀና አማራጮችን ማቅረብ መቻል አለብን፤ በአዲስ ሁኔታ ሁለቱንም ገጽታዎች ማየት እንሞክር:: ምናልባትም በዓለማችን ያለውን ዓመፅ ብዛት ተመልክተን ምንም ማድረግ እንደማንችል ተስፋ ያስቆርጠን ይሆናል:: ይሁን እንጂ የቱንም ያህል ትንሽ ቢመስል እንኳ ለውጥ ለማምጣት ያስችለና ብለን ቆርጠን ከተነሳን የለውጥ ሂደቱ ያኔውኑ ጀምሮል ማለት ይቻላል:: ስለዚህ ማከናውን እችላለሁ ብለህ ከምታስበው አሁኑኑ ጀምር!

## ሌሎችንም አሳትፍ

ከማኅበረ ምዕመንህ ስዎች የምታሳትፋቸው እነማን ናቸው? ብዙ ማኅበረ ምዕመናን የተለያየ አቅምና ዕውቀት ያላቸው ወጣት ወንዶችና ሴቶች አሏቸው:: ዕርቅን በተመለከተ በጥልቀት ማየት የሚችል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ማደራጀት ይቻል ይሆን? የጥቃት ሰለባ የሆኑ ሰዎችን በመርዳት በኩል የቤተ ክርስቲያንህ መጋቢዎች ጉባዔ ምን ማድረግ የሚችለው አለ?



ስለ መከራቸውና መከራውን ስላደረሱባቸው ሰዎች ለሌሎች ማካፈል የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይቻላልን? የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖችን ማሳተፍ እንደሚቻል ሁሉ የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሰዎችንም ማሳተፍ ይቻላልን? በአካባቢህም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ ምን ዓይነት ቡድኖች ተቋቁመዋል? ምን ዓይነት እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል? ከእነርሱ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ማድረግ ይቻላል?

## ጸልይ

መጀመሪያ እኛ ራሳችን ሳንለወጥ ሁኔታዎች እንዲለወጡ የምንጸልይ ከሆነ፤ አንድ ደረጃ ላይ ልባችን መሰበሩ የማይቀር ነው:: ቀደም ሲል ከዚህ የጥናት መመሪያ እንደተመለከትነው እኛ ራሳችን የችግሩና የዓመፃው ተሳታፊዎች ነን እንጂ ዳር ቆመን ተመልካቾች ብቻ አይደለንም:: እንግዲህ ከዚህ አኳያ ስንጸልይ፤ በግለሰብም ሆነ በብያተ ክርስቲያናት ደረጃ ራሳችንን ለእግዚብሔር ግልጽ እናደርጋለን ማለት ነው:: ስለሆነም ከጸለት የምናገኘው መንፈሳዊ ልምምድ እርቅና ሰላምን ማስፈን የሚስችል ሕይወት እንዲኖረን ይረዳናል:: ይህም፤ ከሌሎች ጋር ያለንን ግንኙነት መለወጥ ወይም ማስተካከልንም ይጨምራል:: ሌሎችን ይቅር ማለት አለብን፤ እኛም የሌሎችን ይቅርታ ማግኘት አለብን:: ጸሎት ብርቱ መሣሪያ ነው፤ በተለይ ደግሞ የጥቃት ሰለባ ከሆኑ ወገኖች ጋር ሆነን ስንጸልይ ታላቅ ነገርን ያደርጋል:

## ሐሳብና ዕቅድህን ለብቻህ አታድርግ

ምን እንደ ተማርህና ምን ማድረግ እንዳሰብህ ሌሎችም ይወቁ:: በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ዓመፃን

ማስወገድ የተሰኘው ዕቅድ እውን የሚሆነው በአብያተ ክርስቲያናት ተሳትፎ ነው። ስለዚህም ያለንን ራዕይና እንቅስቃሴ እርስ በርስ መካፈል ይኖርብናል። በዚህ ዕቅድ ስላላችሁ ተሳትፎ ቤተ ክርስቲያኖቻችሁና አብያተ ክርስቲያናቱ ጉባዔ እንዲያውቁ አድርጉ። «ስለ ሰላም ማውራቱ ብቻ በቂ አይደለም፤ ልናምንበትም ይገባል። ማመን ብቻ በቂ አይደለም፤ ለሰላም መሥራትም ይገባል» (ኤሊር ሩዝቬልት)